የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥረኛ ዓመት ቁጥር ፶፭
አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፱ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፬፻፲/፲፱፻፺፮ ዓ.ም
የቅጅና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ አዋጅ
ቁጥር.........ገጽ ፪ሺ፯፻፸፫

## አዋጅ ቁጥር ፬፻፲/፲፱፻፺፮

## የቅጅና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ ለማድረግ የወጣ አዋጅ

የሥነፅሁፍ፣ የኪነጥበብ እና ተመሳሳይ የፈጠራ ስራዎች የአንድን ሀገር ባህላዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ሳይንሳዊና ቴክኖሎጂያዊ ልማትን በማፋጠን ረገድ ትልቅ ሚና የሚጫወቱ በመሆናቸው የሚበረታቱበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠሩ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የሥነፅሁፍ፣ የኪነጥበብና ተመሳሳይ የፈጠራ ስራዎችን ውጤታማ ለማድረግ በሚከናወኑ ስራዎች ላይ ተዛማጅ መብቶችን በሕግ እውቅና መስጠትና ጥበቃ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭/፩/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የቅጅና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር ፬፻፲/፲፱፻፺፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

ያንዱ ዋጋ 6.40
Unit Price

፪ **ትርጓሜ**

**የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፣**

፩/ "የኦዲዮ ቪዥዋል ሥራ" ማለት ለዚሁ ተግባር በተሰራ መሳሪያ በመጠቀም በቀላሉ ሊታይ የሚችል፣ ተከታታይነትና ተዛማጅነት ያለውን በድምፅ የታጀበ ወይም ያልታጀበ የእንቅስቃሴ ስሜትን የሚፈጥሩ ምስሎችን የያዘ ማንኛውም ሥራ ሲሆን ሲኒማቶግራፊንና ሌሎች ፊልሞችን ይጨምራል፣

፪/ "የሥራ አመንጪ" ማለት የአንድን የአእምሮ ውጤት የሆነን ሥራ የፈጠረ ማንኛውም ግለሰብ ሲሆን የሚከተሉትን ይጨምራል፣

ሀ. ሥራው የኮምፒውተር ፕሮግራም ከሆነ የኮምፒውተር ፕሮግራሙን የፈጠረው ግለሰብ፣
ለ. ሥራው ፎቶግራፍ ከሆነ ለጥንቅሩ ኃላፊ የሆነውን ግለሰብ፣

፫/ "ብሮድካስቲንግ" ማለት ድምፅን ወይም ምስልንና ድምፅን ሽቦ አልባ በሆነ መንገድ ለሕዝብ ማሰራጨት ነው፣

፬/ "የብሮድካስቲንግ ድርጅት" ማለት ሬድዮ፣ ቴሌቭዥን እና የኬብል ቴሌቭዥን ጣቢያ ወይም ሳተላይት ነው፣

፭/ "ስብስብ ሥራ" ማለት በአንድ የተፈጥሮ ሰው አነሳሽነትና መሪነት ከሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ግለሰቦች የተፈጠረ እና በሥራው ላይ አስተዋፅኦ ያላቸው ግለሰቦች ሳይጠቀሱ በመሪው ስም ብቻ እንደሚታወቅ ግንዛቤ ተወስዶ የተሰራ ሥራ ነው፣

፮/ "ለህዝብ ማሰራጨት" ማለት የአንድ ሥራ ክወና፣ የድምፅ ሪከርድ ወይም ብሮድካስት ምስል፣ ድምፅ ወይም ሁለቱን በሽቦ ወይም ያለሽቦ ማሰራጨት ሲሆን ምስሉ ወይም ድምፁ በመደበኛው የቤተሰብ ዙሪያ እና የቤተሰቡ የቅርብ ወዳጆች ከሚገኙበት ቦታ ውጪ በሆነ ወይም ስርጭቱ ከሚተላለፍበት በጣም ራቅ ያለ ቦታ ላይ በሚገኝ ሰው ሊሰማ ወይም ሊታይ የሚችል ሆኖ ምስሉ ወይም ድምፁ በአንድ አይነት ቦታና ጊዜ ወይም በተለያዩ ቦታዎች እና ወይም ጊዜያት ሊሰማ ወይም ሊታይ መቻሉ ግምት ውስጥ ሳይገባ ምስሉ ወይም ድምፁ ያለ ስርጭቱ ሊሰማ ወይም ሊታይ የማይችል ሲሆን ነው፣

፯/ "የኮምፒዩተር ፕሮግራም" ማለት በመሳሪያ ተነባቢ የሚሆን አንድ ኮምፒዩተር ተግባሩን እንዲያከናውን ወይም የታለመለትን ውጤት እንዲያመጣ የሚያስችል የቃላት፣ የኮዶች፣ የዘዴዎች፣ ወይም በሌላ አኳኋን የሚገኝ የመመሪያዎች ስብስብ ነው፣



/ "የቅጅ መብት" ማለት ከአንድ ስራ የሚመነጭ የኤኮኖሚ መብት ሲሆን አግባብነት ባለው ጊዜ የሞራል መብቶችን ይጨምራል፣

/ "ፍርድ ቤት" ማለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፣

"ዳታ ቤዝ" ማለት በኮምፒዩተር አማካኝነት ለመፈለግ እንዲቻል ስርአት ባለው አኳኋን የተደራጀ የመረጃ፣ መጣጥፍ፣ ቁጥር ወይም ዲያግራም ስብስብ ነው፣

"መቅረፅ ወይም ግዝፈት እንዲያገኝ ማድረግ" ማለት አንድ ሥራ፣ ምስል፣ ድምፅ ወይም የአንደኛቸው አምሳያ ምትክ ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀ መሣሪያ አማካኝነት እንዲታይ፣ እንዲባዛ፣ ወይም እንዲሰራጭ ማድረግ ነው፣

"በቅጥር የተከናወነ ሥራ" ማለት በቅጥር ወይም በአገልግሎት ውል መሰረት ተከፋይ በሆነ የሥራ አመንጪ የተፈጠረ ሥራ ነው፣

"የሙዚቃ ሥራ" ማለት ሙዚቃ ሲሆን ከሙዚቃው ጋር ሊከወኑ፣ ሊነገሩ ወይም ሊዘመሩ የተዘጋጁ ማናቸውም ቃላትን ወይም ድርጊትን አይጨምርም፣

"ተዛማጅ መብት" ማለት ከዋኝ፣ የድምፅ ሪከርዲንግ ፕሮዲውሰር፣ የብሮድካስቲንግ ድርጅት በሥራው ላይ ያለው መብት ነው፣

"ፅህፈት ቤት" ማለት በአዋጅ ቁጥር ፫፻፳/፲፱፻፺፭ ዓ.ም የተቋቋመው የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ፅህፈት ቤት ነው፣

"የቅጅ መብት ባለቤት" ማለት ኤኮኖሚያዊ መብቱ ለሥራ አመንጪው በሆነ ጊዜ የሥራ አመንጪው፣ ኤኮኖሚያዊ መብቱ ከመጀመሪያው ሥራ አመንጪው ውጪ ላለ ግለስብ ወይም ህጋዊ ሰውነት የተሰጠው አካል ሲሰጥ ግለሰቡ ወይም ህጋዊ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት ወይም የኤኮኖሚ የባለቤትነት መብቱ ለአንድ ግለሰብ ወይም ህጋዊ ሰውነት የተሰጠው አካል ተላልፎ ከሆነ መብቱ የተላለፈለት ግለሰብ ወይም ህጋዊ ሰውነት የተሰጠው አካል ነው፣

"ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም የህግ ሰውነት የተሰጠው አካል ነው፣

"የፎቶግራፍ ሥራ" ማለት አንድ ምስል ለማውጣት ወይም ምስልን በማናቸውም ዘዴ ለማውጣት እንዲቻል ብርሃን እና ወይም ሌላ ጨረርን በማናቸውም የመቀበያ አካል ላይ መቅረፅ ሲሆን ፊልምን አይጨምርም፣

፲፱/ "ከዋኝ" ማለት ተዋናይ፣ ዘፋኝ፣ ዘማሪ፣ ሙዚቀኛ ተወዛዋዥ እና ሌላ ማናቸውም የሚተውን፣ የሚያወጣ፣ የሚጫወት፣ የሚዘፍን፣ የሚያዝናና ወይም በሌላ ማናቸውም አኳኋን የስነፅሁፍና የኪነጥበብ ሥራን የሚከውን ግለሰብ ነው፣

፳/ "ፕሮዲውሰር" ማለት የኦዲዮቪዥዋል ሥራ ለመስራት ሃሳብ ያመነጨና ሥራውን በኃላፊነት የሚያሰራ፡ሰው ነው፣

፳፩/ "የድምፅ ሪከርዲንግ ፕሮዲውሰር" ማለት የድምፅ ሪከርዲንግ ሥራ ለመስራት ሃሳብ ያመነጨና ሥራውን በሀላፊነት የሚያሰራ ሰው ነው፣

፳፪/ "የታተመ ሥራ" ማለት የአንድን ሥራ ወይም የድምፅ ሪከርዲንግ ተጨባጭነት ያላቸው ቅጂዎች በሽያጭ፣ በኪራይ፣ ለህዝብ ውሰት፣ እንዲሁም የቅጅዎችን ባለቤትነት ወይም ይዞታ ለማስተላለፍ እንደሁኔታው በሥራው አመንጪ ወይም በቅጂ ባለመብቱ ወይም በድምፅ ሪከርዲንግ ፕሮዲውሰር ፈቃድ በበቂ መጠን ለህዝብ የቀረበ ሥራ ነው፣

፳፫/ "ለሕዝብ የሚደረግ ውሰት" ማለት በአንድ ሥራ ወይም የድምፅ ሪከርዲንግ ኦሪጂናል ወይም ቅጂው ላይ ያለን የይዞታ መብት በጊዜያዊነት ያለ ትርፍ ሕዝባዊ አገልግሎት በሚሰጡ ቤተመፃህፍት፣ ቤተመዛግብት፣ ወይም ተመሳሳይ ተቋማት ለሕዝብ ማስተላለፍ ነው፣

፳፬/ "ለሕዝብ የቀረበ ክወና" ማለት

ሀ. በግንባር ወይም ማናቸውንም የመገናኛ ዘዴዎች በመጠቀም በመነባነብ፣ በጭውውት፣ በውዝዋዜ፣ በትወና፣ አንድን ሥራ ለህዝብ መከወን፣
ለ. የኦዶዩቪዥዋል ሥራን በተመለከተ ምስል በተከታታይ እንዲታይ፣
ሐ. የድምፅ ሪከርዲንግን በተመለከተ ድምፅ ለህዝብ እንዲሰማ ማድረግ ነው፣

፳፭/ "ማባዛት" ማለት አንድን ሥራ ወይም የድምፅ ሪከርዲንግ በጊዜያዊነት ወይም በቋሚነት የኤሌክትሮኒክ ማከማቻን ጨምሮ በማንኛውም አኳኋን ወይም መልክ ሥራውን ወይም የድምፅ ሪከርዱን በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ቅጅዎች ማራባት ነው፣

፳፮/ "ትክክለኛ ቅጅ" ማለት ፎቶኮፒን በመሳሰሉ ከማተም ውጪ ባሉ መንገዶች የአንድን ሥራ ኦሪጅናል ወይም ቅጂ መጠኑ ይነስም ይደግም በትክክል መገልበጥ ነው፣

፳፯/ "ኪራይ" ማለት ለትርፍ ሲባል አንድ የኦዲዮቪዥዋል ሥራ ወይም የኮምፒዩተር ፕሮግራም ወይም የድምፅ ሪከርዲንግ ወይም ግዝፈት ያለው ክወና ይዞታ በጊዜያዊነት ማስተላለፍ ነው፣



፳፰/ "የድምፅ ሪከርዲንግ" ማለት የክወና ድምፅ ወይም ሌላ ድምፅ ወይም አምሳያ ምትክ ግዝፈት ያገኘበት ዘዴን ወይም ድምፁ የተቀረፀበትን አካል ግምት ውስጥ ሳይገባ ክዋኔ ወይም ድምፅ ወይም አምሳያው ግዙፍነት እንዲያገኝ ማድረግ ሲሆን የኦዲዮቪዥዋል ሥራን፣ የድምፅ ትራክን የመሳሰሉ የድምፅና ምስል ግዝፈትን አይጨምርም፣

፳፱/ "የጋራ የባለቤትነት ሥራ" ማለት ከሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ የሥራ አመንጪዎች አስተዋፅኦ ያበረከቱበት የፈጠራ ሥራ ሲሆን በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፳) መሰረት የስብስብ ሥራ ያልሆነ ሥራ ነው፣

፴/ "ሥራ" ማለት የሥነ ፅሁፍ፣ ኪነጥበብ እና ሳይንሳዊ መስኮች ውጤት ሆኖ በተለይ የሚከተሉትን ይጨምራል፣

ሀ. መፅሐፍ፣ ቡክሌት፣ በመፅሄት ወይም በጋዜጣ ላይ የሚገኝ መጣጥፍ፣ የኮምፒውተር ፕሮግራም፣
ለ. ንግግር፣ ሌክቸር፣ ለአንድ ለተወሰነ ክፍል የሚደረግ መልእክት አዘል ንግግር፣ የሃይማኖት ስብከት፣ እና ሌላ በቃል የቀረበ ሥራ፣
ሐ. ድራማ፣ ድራማዊ የሙዚቃ ሥራ፣ በእንቅስቃሴ ብቻ የሚቀርብ ድራማ (ፓንቶማይምስ) የመድረክ ውዝዋዜ እና ሌላ ለመድረክ ተብሎ የሚሰራ ሥራ፣
መ. የሙዚቃ ሥራ፣
ሠ. የኦዲዮቪዥዋል ሥራ፣
ረ. የኪነ ህንፃ ሥራ፣
ሰ. የስዕል፣ የቅብ፣ የሀውልት፣ የቅርፃ ቅርፅ፣ የህትመት፣ የፊደል ቅርፅ ጥልፍ እና ሌላ የስነጥበብ ሥራ፣
ሸ. የፎቶግራፍ ስራ፣
ቀ. ስዕላዊ መግለጫ፣ ካርታ፣ ፕላን፣ ንድፍ እና ባለ ሶስት ገፅታ ከጂኦግራፊ፣ ቶፖግራፊ፣ ኪነ ህንፃ ወይም ሳይንስ ጋር የተያያዘ ሥራ፣

## የተፈፃሚነት ወሰን

፩/ በዚህ አዋጅ የሚደረገው የህግ ጥበቃ፣

ሀ. ኢትዮጵያዊ ዜግነት ባለው ወይም ቋሚ መኖሪያው ኢትዮጵያ ውስጥ የሆነ የሥራ አመንጪ ሥራ፣
ለ. የስራ አመንጪው ዜግነት ወይም ቋሚ መኖሪያ ግምት ውስጥ ሳይገባ በኢትዮጵያ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ በታተመ ወይም በውጭ ሀገር ለመጀመሪያ ጊዜ በታተመና በ፴ ቀናት ውስጥ ኢትዮጵያ ውስጥ በታተመ ሥራ፣
ሐ. የፕሮዲውሰሩ ዋና መሥሪያ ቤት ወይም ቋሚ መኖሪያ ኢትዮጵያ ውስጥ የሆነ የኦዲዮቪዥዋል ሥራ፣ እና

መ. በኢትዮጵያ ውስጥ የተገነባ የኪነ ህንፃ ሥራ ወይም በኢትዮጵያ ውስጥ በቆመ ህንፃ ወይም ሌላ ስትራክቸር ውስጥ የተካተተ የኪነጥበብ ሥራ፣

ላይ ተፈፃሚ ይሆናል::

፪/ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ኢትዮጵያ በፈረመቻቸው አለም አቀፍ ስምምነቶች ወይም ኮንቬንሽኖች መሰረት ጥበቃ ባገኙ ስራዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ፣

፫/ የከዋኞች ጥበቃን የሚመለከቱ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች፣

ሀ. ኢትዮጵያዊ ዜግነት ባለው ከዋኝ፣

ለ. በውጭ ዜጎች፣

i. በኢትዮጵያ ውስጥ የተከወነ፣

ii. በዚህ አዋጅ ጥበቃ ባገኘ የድምፅ ሪኮርዲንግ ውስጥ የተካተተ ወይም፣

iii. በድምፅ ሪኮርዲንግ ውስጥ ግዙፍነት የሌለው ቢሆንም በዚህ አዋጅ ጥበቃ ባገኘ ብሮድካስት ውስጥ የተካተተ ክውና፣

ላይ ተፈፃሚ ይሆናል::

፬/ የድምፅ ሪኮርዲንግ ጥበቃን በተመለከተ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች፣

ሀ. በኢትዮጵያውያን ፕሮዲውሰሮች የተዘጋጀ የድምፅ ሪኮርዲንግ፣

ለ. ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ ግዝፈት ባገኘ የድምፅ ሪኮርዲንግ፣

ሐ. ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ በታተመ የድምፅ ሪኮርዲንግ፣

ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ::

፭/ የብሮድካስት ጥበቃን በተመለከተ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች፣

ሀ. ዋና መሥሪያ ቤቱ ኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኝ የብሮድካስቲንግ ድርጅት ብሮድካስት፣

ለ. በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ አሰራጭ የሚያስተላልፈው ብሮድካስት፣ ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ::

፮/ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ኢትዮጵያ ባፀደቀቻቸው አለም አቀፍ ኮንቬንሽኖችና ስምምነቶች መሰረት ጥበቃ ባገኙ ከዋኞች፣ የድምፅ ሪኮርድ ፕሮዲውሰሮች እና የብሮድካስቲንግ ድርጅቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ፣

፯/ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች በቅጅና ተዛማጅ መብቶች ላይ ሥራው የታቀፈበትን ቁሳዊ ነገር የባለቤትነት መብት አያጠቃልልም::



፬. <u>የመጀመሪያ ሥራን መሰረት ያደረገ ሥራ</u>

፩/ የሚከተሉት እንደ ሥራ ጥበቃ ይደረግላቸዋል፣

ሀ. ትርጉም፣ የማመሳሰል ስራ፣ ቅንብር እና ሌላ የስራውን አይነት የሚቀይር ወይም የሚያሻሽል ሥራ፣

ለ. በይዘት፣ በቅንብር ወይም በአመራረጥ የተነሳ ኦሪጅናል የሆነና በሚነበብ መሳሪያ ወይም በሌላ መልክ ያለ ኢንሳይክሎፒዲያ፣ የቅኔ ስብስብ ወይም ዳታቤዝን የመሳሰለ የስብስብ ሥራ፣

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተመለከተው ጥበቃ የመጀመሪያ ስራን መሰረት ያደረገ ሥራ ለመስራት ጥቅም ላይ ለዋለ ወይም በዚሁ ሥራ ውስጥ ለተካተተ የቀድሞ ሥራ ላይ ያለን ጥበቃ አያስቀረውም፣

፭. <u>ጥበቃ የማይደረግላቸው ስራዎች</u>

በዚህ አዋጅ በአንቀፅ ፪፣ ፫ እና ፬ የተደነገገው ቢኖርም የሚከተሉት ጥበቃ አይደረግላቸውም፣

ሀ. ማንኛውም ሀሳብ፣ የአሰራር ሂደት፣ ሲስተም፣ የአሰራር ዘዴ፣ ፅንሰ ሀሳብ፣ ቀመር፣ ለአጠቃላይ ሥራ የሚያገለግል የቁጥር ሰንጠረዥና ቅፅ፣ መርህ፣ በአንድ ሥራ ውስጥ የተብራራ፣ የተገለፀ፣ የተተነተነ ወይም የተነገረ ሆነም አልሆነ ግኝት ወይም ዳታ፣

ለ. የህግ ባህሪ ያላቸው ማናቸውም ይፋ የሆኑ የህግ እና የአስተዳደር ሰነዶችና ይፋ የሆነ ትርጓሜ ያቸው፣

ክፍል ሁለት

<u>ጥበቃ ለማግኘት የሚያስፈልጉ መመዘኛዎች፣ የብቸኝነት መብት አይነትና የተፈፃሚነት ወሰን</u>

፮. <u>ጥበቃ ለማግኘት የሚያስፈልጉ መመዘኛዎች</u>

፩/ በዚህ አዋጅ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የሥራ አመንጪ የሥራው አላማና የጥራት ደረጃ ግምት ውስጥ ሳይገባ፣

ሥራው፣

ሀ. ወጥ (ኦርጅናል) ከሆነ፣

ለ. ከተቀረፀ ወይም ግዙፍነት ካገኘ፣

ሥራውን በማውጣት ምክንያት ብቻ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ጥበቃ ያገኛል::

፪/ የፎቶግራፍ ሥራዎች ጥበቃ የሚያገኙት በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) ከተመለከተው መመዘኛ በተጨማሪ፣

ሀ. የአንድ ስብስብ አካል ሲሆኑ ወይም በመፅሐፍ መልክ ሲታተሙ ወይም፣

ለ. የሥራ አመንጪውን ወይም ወኪሉን ስምና አድራሻ ሲይዙ፣

ይሆናል::

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (፩) ለሥራ አመንጪ የተሰጠው ጥበቃ በዚህ አዋጅ የድምፅ ሪከርዲንግ ፕሮዲውሰር፣ ብሮድካስተር ወይም ከዋኝ በሚያገኙት መብት ቀሪ አይሆንም::

## ፯. ኢኮኖሚያዊ መብቶች

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፱ እስከ ፲፱ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የሥራ አመንጪ ወይም የአንድ ሥራ ባለቤት የሚከተሉትን ለመፈፀም ወይም ሌላ ሰው እንዲፈፅማቸው ለመፍቀድ ብቸኛ መብት ይኖረዋል፣

ሀ. ሥራን የማባዛት፣
ለ. ሥራን የመተርጎም፣
ሐ. ሥራን የማመሳሰል፣ የማቀናበር ወይም ወደ ሌላ አይነት የመቀየር፣
መ. በሽያጭ ወይም በኪራይ አርጅናል ሥራን ወይም ቅጂውን የማከፋፈል፣
ሠ. አርጅናል ሥራን ወይም ቅጂውን ከውጭ ሀገር የማስገባት፣
ረ. አርጅናል ሥራን ወይም ቅጂውን ለህዝብ የማሳየት፣
ሰ. ሥራን በይፋ የመከወን፣
ሸ. ሥራን ብሮድካስት የማድረግ፣
ቀ. ሥራን በሌላ መንገድ የማስራጨት

፪ የኮምፒውተር ፕሮግራሙ የኪራይ ወይም የህዝብ ውስት መሰረታዊ አካል ካልሆነ በቀር በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) (መ) ላይ የተደነገገው በኮምፒውተር ፕሮግራም ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፣

፫/ የአንድ ወጥ የስነ ጥበብ ስራ ወይም የአንድ ደራሲ ወይም የዜማ ደራሲ አርጅናል ፅሁፍ በሥራው አመንጪ ከተላለፈ በኋላ ከሚደረገው ድጋሚ ሽያጭ ዋጋ ላይ የሥራ አመንጪው ወይም ወራሹ የተወሰነ ድርሻ የማግኘት መብት ይኖረዋል:: የክፍያው መጠንና የተፈፃሚነት ሁኔታ በዚህ አዋጅ ስር በሚወጣው ደንብ ይወሰናል::

## ፰. የሞራል መብት

፩/ የሥራ አመንጪው የኢኮኖሚ መብት ባለቤት ቢሆንም ባይሆንም የሚከተሉት የሞራል መብቶች አሉት::

ሀ. ወቅታዊ ሁኔታን በብሮድካስት አማካኝነት ለመዘገብ ባጋጣሚ ወይም በድንገት ከተካተተ ሥራ ውጪ የሥራ አመንጪነቱ እንዲታወቅ የመጠየቅ፣
ለ. ሳይታወቅ የመቆየት ወይም የብዕር ስም የመጠቀም፣ እና
ሐ. ክብሩንና መልካም ስሙን የሚያጎድፍ የሥራ መዛባት፣ መቆራረጥ ወይም በሌላ መልክ መቀየርን የመቃወም፣
መ. ሥራን የማሳተም፣



፪ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተዘረዘሩት መብቶች በህግ መሠረት ለወራሾች ወይም ለስጦታ ተቀባዮች ካልሆነ በቀር የሥራ አመንጪው በህይወት እያለ ወደ ሶስተኛ ሰው ሊተላለፉ አይችሉም፣

፫/ ሥራ አመንጪው፣ ወራሽና ስጦታ ተቀባይ

ሀ. ያነሳውን መብትና የመብት መነሳቱ ተፈፃሚ የሚሆንበትን ሁኔታ በፅሁፍ በማመልከት፣

ለ. በሥራው ላይ የሚደረግ ማሻሻል የሚኖረውን ባህሪና የለውጥ መጠን በመግለፅ፣
በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተዘረዘሩትን መብቶች ሊተው ይችላል::

፬/ የሞራል መብቶች የሥራ አመንጪው ከሞተ በኋላ ኢኮኖሚያዊ መብቶች ፀንተው ለሚቆዩበት ጊዜ ጥበቃ ይደረግላቸዋል::

## ፱. ለግል አገልግሎት ሥራን ስለማባዛት

፩ በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፯ (፩) (ሀ) የተደነገገው ቢኖርም የቅጅ መብት ባለቤቱ የታተመ ሥራን አንድ ቅጅ ለግል ጥቅም ፍጆታ ለማዋል ማባዛትን አይከለክልም፣

2/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተደነገገው ቢኖርም፣

ሀ. በህንፃ ወይም በኮንስትራክሽን መልክ የሚገኝ የኪነ ህንፃ ሥራን፣
ለ. በኖታ መልክ የሚገኝ የሙዚቃ ስራን ወይም በአመንጪው የተፈረመ አሪጅናል ወይም ቅጅ የስነ ጥበብ ሥራን፣
ሐ. በሙሉ ወይም በአመዛኙ በዲጂታል መልክ የተቀመጠ ዳታ ቤዝን፣
መ. በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፲፬ ከተደነገገው ውጪ የኮምፒዩተር ፕሮግራምን ወይም፣
ሠ. የሥራ አመንጪው ህጋዊ ጥቅም ወይም የተለመደ አጠቃቀም ተገቢ ባልሆነ ሁኔታ የሚጎዳ ሥራን፣

ማባዛት አይቻልም::

## ፲: ጥ ቅ ስ

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፯ (፩) (ሀ) የተደነገገው ቢኖርም ከአንድ ከታተመ ሥራ ጥቅስ እንዳይጠቀስ የቅጅ መብት ባለቤቱ ሊከለክል አይችልም፣

፪/ ጥቅሱ ከተገቢ አሰራርና አላማው ከሚጠይቀው በላይ መሆን የለበትም፣

፫/ ጥቅሱ የተወሰደው የሥራው አመንጪውን ስም ከያዘ ሥራ ሲሆን የጥቅሱን ምንጭና የሥራውን አመንጪ ስም መጥቀስ አለበት::

**፲፩. ለማስተማር ስራ ስለሚደረግ ማባዛት**

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፯ (፩) (ሀ) የተደነገገው ቢኖርም የቅጅ መብት ባለቤቱ ከተገቢ አሰራርና አላማው ከሚጠይቀው በላይ እስካልሆነ ለማስተማሪያነት ወይም ለማብራሪያ የሚውል የታተመ ሥራ ወይም የድምፅ ሪከርዲንግ እንዳይባዛ ሊከለክል አይችልም፣

፪/ በዚህ አንቀፅ መሰረት የተደረገ ቅጂ እስከተቻለ ድረስ በማንኛውም ጊዜ የተባዛውን ሥራ ወይም የድምፅ ሪከርዲንግ ምንጭና የአመንጪው ስም መጥቀስ አለበት::

**፲፪. <u>በቤተመፃህፍት፣ በቤተመዛግብት ወይም መሰል ተቋማት ስለሚደረግ ማባዛት</u>**

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፯ (፩) (ሀ) ቢኖርም የቅጅ መብት ባለቤቱ ለትርፍ ባልቆመ ቤተመፃህፍት፣ ቤተመዛግብት ወይም መሰል ተቋማት የሚደረግ የማባዛት ተግባርን ሊከለክል አይችልም፣

፪/ አንድ ቤተመፃህፍት፣ ቤተመዛግብት ወይም መሰል ተቋም በግለሰብ ጥያቄ የታተመን መጣጥፍ፣ አጭር ሥራ ወይም ከአንድ ሥራ ላይ የተወሰደ ቅንጫቢ ሥራን ማባዛት የሚችለው፣

ሀ. ቅጂው ለትምህርት፣ ለጥናት፣ ለስኮላርሺፕ ወይም ለምርምር እንደሚውል በቤተመፃህፍት፣ በቤተመዛግብት ወይም መሰል ተቋም ሲረጋገጥ፣

ለ. ሥራው ለአንድ ጊዜ ብቻ የሚባዛ ከሆነ፣ የሚደጋገም ከሆነም በተያዩና ተዛማጅነት በሌላቸው ሁኔታዎች የሚፈፀም ከሆነ፣

ሐ. ሥራው እንዲባዛ ፈቃድ የሚሰጥ አስተዳደራዊ አካል የሌለ ከሆነ ብቻ ይሆናል::

፫/ በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (፩) የተመለከተው የቅጅ ሥራ የሚከናወነው፣

ሀ. የአንድ ሥራን ቅጅ ለመጠበቅ ወይም ለመተካት አስፈላጊ ሲሆን ወይም በሌላ ተመሳሳይ ቤተመፃህፍት ወይም ቤተመዛግብት ቋሚ ስብስብ ውስጥ የነበረ፣ የጠፋ፣ የተበላሸ ወይም አገልግሎት መስጠት የማይችል ሲሆን፣

ለ. በደህና ሁኔታ ያለን ቅጅ ለማግኘት የማይቻል ሲሆን፣

ሐ. የማባዛቱ ተግባር አንድ ጊዜ ብቻ የተፈፀመ ሲሆን፣ የሚደጋገም በሆነ ጊዜም በተለያዩና በማይዛመዱ ሁኔታዎች ሲሆን፣

ብቻ ይሆናል::



**፲፫. <u>ለህዝብ መረጃ አገልግሎት አላማ ማባዛት፣ ብሮድካስት ማድረግና ማሰራጨት</u>**

በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፯(፩) (ሀ)፣ (ሸ) እና (ቀ) የተደነገገው ቢኖርም እስከተቻለ ድረስ የሥራውን ምንጭና የሥራ አመንጪውን ስም መጥቀስ እንደተጠበቀ ሆኖ የቅጅ መብት ባለቤቱ፣

፩/ የማባዛት፣ ብሮድካስት የማድረግ ወይም ለህዝብ የማሰራጨት መብቱ የሥራው አመንጪ ወይም የቅጅ ባለመብቱ መሆኑን በቅጅው ላይ በግልፅ የተጠቀሰ ነገር ከሌለ በወቅታዊ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ ወይም የሃይማኖት ጉዳዮች ላይ በጋዜጣ፣ በመፅሄት የወጡ ወይም ተመሳሳይ ባህሪ ኖሯቸው ብሮድካስት የተደረጉ መጣጥፎችን በሌላ ጋዜጣ ወይም መፅሄት ማባዛትን፣ በብሮድካስቲንግ ወይም በሌላ የመገናኛ ብዙሃን ለህዝብ ማድረስን፣

፪/ ወቅታዊ ሁኔታን ለመዘገብ ሲባል በአንድ በታየ ወይም በተሰማ ጉዳይ ላይ የተዘጋጀ በአጭሩ የተወሰደ ሥራን ማባዛት ወይም ብሮድካስት ማድረግን ወይም በሌላ የመገናኛ ብዙሃን ለህዝብ ማድረስን፣

፫/ የፖለቲካ ንግግርን፣ ሌክቸርን፣ ስብከትን ወይም ተመሳሳይ ባህርይ ያለው ሌላ ሥራን ወይም በፍርድ ሂደት ላይ የተደረገ ንግግርን ወቅታዊ መረጃ ለህዝብ ለመስጠት በጋዜጣ ወይም በመፅሄት ማባዛት፣ ብሮድካስት ማድረግን ወይም በሌላ የመገናኛ ብዙሃን ለህዝብ ማቅረብን፣

ሊከለክል አይችልም::

**፲፬. <u>የኮምፒዩተር ፕሮግራም ስለማባዛትና ስለማሻሻል</u>**

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፯ (፩) (ሀ) እና (ሐ) የተደነገገው ቢኖርም የቅጅ መብቱ ባለቤት የኮምፒዩተር ፕሮግራምን ነጠላ ቅጅ ማድረግን ወይም ማሻሻን ሊከለክል አይችልም፣

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተመለከተውን የኮምፒዩተር ፕሮግራም ማሻሻል ወይም ማባዛት የሚቻለው፣

ሀ/ የኮምፒዩተር ፕሮግራሙ ለታሰበለት አላማና አገልግሎት እንዲውል በኮምፒዩተር ለመጠቀም፣

ለ/ የወደፊት አጠቃቀምን ማረጋገጥ አስፈላጊ በመሆኑ በኮምፒዩተር ፕሮግራሙ የመጠቀም መብት ያለው ሰው መጠባበቂያ ቅጅ ሲፈልግ ወይም፣

ሐ/ የኮምፒዩተር ፕሮግራም የተሰራበትን አላማና ያለውን አቅም መሠረት በማድረግ ከኮምፒዩተር ጋር ተጣጥሞ እንዲሰራ የፕሮግራሙን አጠቃቀም ማሻሻል የግድ ሲሆን፣

ነው::

## ፲፭. ለግል አገልግሎት አሳማ ወደ አገር ውስጥ ማስገባት

በዚህ አዋጅ በአንቀፅ ፯(፩) (ሠ) የተደነገገው ቢኖርም የቅጅ መብት ባለቤቱ የአንድ ሥራ ቅጅን ለግል አገልግሎት ከውጪ አገር ወደ አገር ውስጥ ማስገባትን መከልከል አይችልም።

## ፲፮. በግልና ያለ ዋጋ የሚደረግ ክውና

በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፯(፩) (ሰ) የተደነገገው ቢኖርም የቅጅ መብት ባለመብቱ በቤተሰብ ወይም በአንድ ትምህርት ቤት ውስጥ ያለ ዋጋ የሚደረግ ሥራን የመከወን ተግባር መከልከል አይችልም።

## ፲፯.. የግዴታ ፈቃድ ስለመስጠት

፩/ የቅጅ መብት ባለቤቱ ወይም ወራሽ ወይም ስጦታ ተቀባይ ተቃውሞ ቢያቀርብም ፅህፈት ቤቱ ለህዝቡ ጥቅም ሲል አንድ የታተመ ሥራ እንዲባዛ፣ እንዲተረጎም ወይም ብሮድካስት እንዲደረግ ሊፈቅድ ይችላል፣

፪/ ፈቃድ የሚሰጥበት ሁኔታና ፎርም በተለይም ለቅጅ መብት ባለቤቱ የሚሰጠው ተገቢ የሆነ ካሳ በደንብ ይወሰናል፣

3/ ፅህፈት ቤቱ በዚህ አንቀፅ በተመለከተው ሥራ ላይ ለውጥ እንዲደረግ ሊፈቅድ አይችልም""

## ፲፰. ሥራን ለህዝብ እይታ ስለማቅረብ

ያለ ሥራ አመንጪው ወይም የቅጅ መብት ባለቤቱ ፈቃድ የአንድ ሥራን ኦሪጅናል ወይም ቅጂ ለህዝብ ማቅረብ የሚቻለው እይታው ከፊልም ስላይድ፣ ከቴሌቪዥን ምስል ወይም በሌላ ማናቸውም ስክሪን ወይም ከሌላ ማናቸውም መሳሪያ ወይም ሂደት ውጪ በሆነ መንገድ ሲቀርብ እና ሥራው የታተመ ሲሆን ወይም የኦርጅናል ሥራው ወይም ቅጂው በሥራ አመንጪው ወይም በወራሹ የተሸጠ ወይም ለሶስተኛ ሰው የተሰጠ ወይም በሌላ ማናቸውም አኳኋን የተላለፈ ሲሆን ነው።

## ፲፱. ቅጅን ስለማሰራጨት

አንድ የታተመ ሥራ ቅጅ ለህዝብ የተሸጠ ሲሆን ቅጅው ያለፈቃድ ወይም ከፍያ በሽያጭ መልክ እንደገና ሊሰራጭ ይችላል።

## ፳. የኢኮኖሚ መብቶች ፀንተው የሚቆዩበት ጊዜ

፩/ የኢኮኖሚ መብቶች የሥራ አመንጪው በህይወት በሚቆይበት ዘመንና ከሞተ በኋላ ለወራሾቹ እስከ ሃምሳ ዓመት ፀንተው ይቆያሉ፣



፪/ በጋራ የሥራ አመንጪዎች የተሠራ ሥራን በሚመለከት ጉዳይ የ፶ ዓመቱ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው የመጨረሻው የሥራ አመንጪው ከሞተበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፣

፫/ የሥራው አመንጪው ከሞተ በኋላ የታተመ ሥራ የ፶ ዓመት የጥበቃ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው ሥራው ከታተመበት ጊዜ ጀምሮ ይሆናል፣

፬/ አንድ ከኦዲዮቪዥዋል ሥራ ውጪ የሆነ ስብስብ ሥራ ኢኮኖሚያዊ መብት ፀንቶ የሚቆየው ሥራው ከተሰራበት ወይም መጀመሪያ ለህዝብ ከቀረበበት ወይም መጀመሪያ ከታተመበት ጊዜ የመጨረሻ ከሆነው አንዱ ጀምሮ ለሃምሳ ዓመት ይሆናል፣

፭/ ሥራው የአመንጪውን ስም ካልያዘ ወይም በብዕር ስም የታተመ ከሆነ የሥራ አመንጪው ኢኮኖሚያዊ መብት ፀንቶ የሚቆየው ሥራው ከተሰራበት ወይም መጀመሪያ ለህዝብ ከቀረበበት ወይም መጀመሪያ ከታተመበት ጊዜ የመጨረሻ ከሆነው አንዱ ጀምሮ ለ፶ ዓመታት ይሆናል፣

፮/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፭) ከተመለከተው ጊዜ በፊት የሥራው አመንጪ ማንነት ከታወቀ ወይም የማያጠራጥር ከሆነ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) እና (፪) እንደ ሁኔታው ተፈፃሚ ይሆናል፣

፯/ በፎቶግራፍ ስራ ላይ ያሉ ኢኮኖሚያዊ መብቶች ፀንተው የሚቆዩት ሥራው ከተሰራበት ጊዜ ጀምሮ ለሃያ አምስት ዓመት ይሆናል፣

፰/ በኦዲዮቪዥዋል ሥራ ላይ ያለ ኢኮኖሚያዊ መብት ፀንቶ የሚቆየው ሥራው ከተሰራበት ወይም ለህዝብ ከተሰራጨበት ጊዜ የመጨረሻ ከሆነው አንዱ ጀምሮ ለሃምሳ ዓመት ይሆናል፣

# ክፍል ሶስት
# የመብት ባለቤትነትና የህግ ግምቶች

## ፳፩. ስለ መጀመሪያ ኢኮኖሚያዊ መብት ባለቤትነት

፩/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፪) እስከ (6) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የአንድ ሥራ አመንጪ የኢኮኖሚያዊ መብቶች የመጀመሪያ ባለቤት ይሆናል፣

፪/ አንድ ሥራ በበርካታ የሥራ አመንጪዎች የተሰራ ሲሆን የኢኮኖሚያዊ መብቶች የመጀመሪያ ባለቤቶች የጋራ ሥራ አመንጪዎች ይሆናሉ፣

፫/ አንድ ሥራ የስብስብ ሥራ ሲሆን ሥራው እንዲሰራ ያመነጨውና የአመራር አቅጣጫ የሰጠው ሰው የኤኮኖሚያዊ መብቶች የመጀመሪያ ባለቤት ይሆናል፣

፬/ አንድ ሥራ በተቀጠረ ወይም የአገልግሎት ክፍያ በተከፈለው ሰው የተሰራ ሲሆን ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ በቀር የኤኮኖሚያዊ መብቶች የመጀመሪያ ባለቤት ቀጣሪው ወይም ስራውን እንዲሰራ ያደረገው ሰው ይሆናል፣

፭/ ሥራው የኦዲዮቪዡዋል ሥራ ከሆነ፣

ሀ. ፕሮዲውሰሩ የኤኮኖሚያዊ መብቶቹ ባለቤት ይሆናል:: ሆኖም እስክሪፕት ፀሀፊው፣ ዳይሬክተሩ፣ የካሜራ ባለሙያው፣ የዜማ ደራሲው፣ ሌሎች የሥራ አመንጪው በሥራው ላይ የሥራ አመንጪነት መብትና ከፕሮዲውሰሩ ጋር በሚያደርጉት ውል መሠረት ክፍያ የማግኘት መብት ይኖራቸዋል፣

ለ. በኦዲዮቪዡዋል ሥራ የተካተተና በነጣላ ጥቅም ላይ የሚውል የስክሪን ፅሁፍ፣ የሙዚቃ ሥራ እንዲሁም ሌላ ሥራ አመንጪ ራሱን ችሎ በቅጅ መብቱ የመገልገል መብት ይኖረዋል::

፮/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፭) የተደነገገው ቢኖርም የኦዲዮቪዡዋል ሥራ ክፍል የሆኑትን ወይም ተሻሽለው የተካተቱትን አስቀድመው የነበሩ ሥራዎችን የሰሩ የሥራ አመንጪዎች ከአስተዋፅኦቸው ወይም አስቀድሞ ከነበረው ሥራ የሚመነጩ ኤኮኖሚያዊ መብቶች ከኦዲዮቪዡዋል ሥራው ከሚመነጩ መብቶች ተለይተው እንደ ቅደም ተከተላቸው ባድረጉት አስተዋፅኦ ወይም ቀዳሚ ሥራቸው ላይ ኤኮኖሚያዊ መብታቸው የተጠበቀ ይሆናል::

፳፪. <u>የሥራ አመንጪነት ግምትና ውክልና</u>

፩/ ተቃራኒ ማስረጃ ካልቀረበ በቀር ሥራው በስሙ የታተመ ሰው የሥራው አመንጪ ተደርጎ ይቆጠራል፣

፪/ የሥራ አመንጪው የብዕር ስም የሚጠቀም ቢሆንም ስለማንነቱ የሚያስጠረጥር ሁኔታ ከሌለ በቀር በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተመለከተው ግምት የሚያስገኘውን ጥቅም መጠየቅ ይችላል፣

፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) እና (፪) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ስሙ በሥራ ላይ የተጠቀሰው አሳታሚ ተቃራኒ ማስረጃ ካልቀረበ በቀር የሥራ አመንጪውን እንደወከለ ተቆጥሮ የሥራ አመንጪውን የኤኮኖሚያዊ እና የሞራል መብቶች ተጠቃሚ ይሆናል:: ይህ ግምት የሥራ አመንጪው ማንነቱን ሲያሳውቅ ተፈፃሚነት አይኖረውም::



## ክፍል አራት
## ኤኮኖሚያዊ መብት ስለማስተላለፍና ፈቃድ ስለመስጠት

### ፳፫. መብት ስለማስተላለፍና ፈቃድ ስለመስጠት

፩/ የቅጅ መብት ባለመብቱ ኤኮኖሚያዊ መብቱን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ማስተላለፍ ወይም በፈቃድ መስጠት ይችላል፣

፪/ ማንኛውም ኤኮኖሚያዊ መብት በሥራ አመንጪው ወይም በቅጅ መብት ባለቤቱ የሚተላለፈው ወይም ፈቃድ የሚሰጠው በፅሁፍ ይሆናል፣

፫/ ማንኛውንም ኤኮኖሚያዊ መብት ማስተላለፍ ወይም በፈቃድ መስጠት በግልፅ ያልተመለከተን መብት መተላለፍን ወይም መፍቀድን እንደጨመረ አይቆጠርም::

### ፳፬. መብት የማስተላለፍ ወይም የፈቃድ ወሰን

፩/ ኤኮኖሚያዊ መብትን የማስተላለፍ ወይም በፍቃድ የመስጠት ወሰን በስምምነት የተመለከተውን መብት በመገልገል ወይም በመጠቀም የተገደበ ይሆናል፣

፪/ የቅጅ መብት ባለቤቱ ወይም ኢኮኖሚያዊ መብቱ የተላለፈለት ወይም በፈቃድ የተሰጠው ሰው መብት ሥራው የታቀፈበትን ቁሳዊ ነገር የባለቤትነት መብትን አያጠቃልልም፣

፫/ በአንድ በተወሰነ የኤኮኖሚ መብት መተላለፍ ወይም መፈቀድ ላይ የተደረሰው ስምምነት የመብት መተላለፉ ወይም ፈቃዱ ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ ሳይወሰን ሲቀር የመብት መተላለፉ ወይም ፈቃዱ እንደቅደም ተከተሉ ከ፲ ወይም ከ፭ ዓመት በኋላ ይሆናል፣

፬/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፪) የተመለከተው ስምምነት መብቱ ሥራ ላይ የሚውልበት መንገድ ወይም ዘዴ በግልፅ ሳያመለክት ከቀረ መብቱ የተላለፈለት ወይም ፈቃድ ተቀባዩ ተዋዋይ ወገኖች በጋራ ያላቸውን ዓላማ ለማሳካት አስፈላጊ የሆኑ ዘዴዎችና መንገዶች በመጠቀም መብቱን ሥራ ላይ ሊያውል ይችላል::

### ፳፭. በኤኮኖሚያዊ መብቶች ስላለመጠቀም

፩/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፪) እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ የኤኮኖሚያዊ መብት የተላለፈለት ወይም የብቸኝነት ፈቃድ ያገኘ ሰው በመብቱ ሙሉ በሙሉ ወይም በበቂ ካልተጠቀመበት እና በዚህም ምክንያት የሥራ አመንጪው ህጋዊ ጥቅም የተጎዳ ሲሆን የሥራ አመንጪው የመብቱን መተላለፍ ወይም ፈቃዱን ሊሽር ይችላል፣

፪/ የተላለፈው ወይም የተፈቀደው መብት ሙሉ በሙሉ ወይም በበቂ ሁኔታ ሥራ ላይ ያልዋለው በዋነኛነት የሥራ አመንጪው መፍትሄ ሊሰጥ የሚችልባቸው ሁኔታዎች ተከስተው ከሆነ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተመለከተው ስምምነት የመሻር መብት ተፈፃሚ አይሆንም፣

፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተመለከተው የስምምነት መሻር መብቱ ከተላለፈበት ወይም ፈቃድ ከተሰጠበት ቀን ወይም ሥራው ከዚህ ቀን በኋላ መብቱ ለተላለፈለት ወይም ፈቃድ ለተሰጠው ሰው ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ባሉት ፫ ዓመታት ውስጥ ተፈፃሚ አይሆንም፣

፬/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተጠቀሰው የመሻር መብት በቅድሚያ ሊነሳ አይችልም::

## ክፍል አምስት
## ስለከዋኝ፣ ድምፅ ሪከርዲንግ ፕሮዲውሰርና ብሮድካስቲንግ ድርጅት መብት ጥበቃ

### ፳፮. የከዋኝን ፈቃድ የሚጠይቁ ድርጊቶች

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፴፪ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ ከዋኝ የሚከተሉትን ለማድረግ ወይም ሌሎች እንዲፈፅሙት ለመፍቀድ ብቸኛ መብት ይኖረዋል፣

ሀ. ብሮድካስቲንጉ ወይም ሌሎች ለህዝብ የሚሰራጩ ነገሮች፣

i. ከዋኙ እንዲሰራ በፈቀደው መሠረት ግዙፍነት እንዲያገኝ ካልተደረገ ወይም፣

ii. ክዋኔውን በመጀመሪያ ብሮድካስት ያደረገው ድርጅት በፈቀደው መሠረት እንደገና ብሮድካስት ካልተደረገ በቀር ክዋኔውን ብሮድካስት የማድረግ ወይም በሌላ መገናኛ መሳሪያ ለህዝብ የማሰራጨት፣

ለ. ግዙፍነት የሌለውን ክዋኔ ግዙፍነት እንዲኖረው የማድረግ፣

ሐ. በማንኛውም መልክ ወይም አኳኋን ግዙፍነት እንዲኖረው የተደረገን ክዋኔ ማባዛት፣

መ. በቅድሚያ ግዙፍነት ያገኘን ክዋኔ ወይም ቅጅውን በሽያጭ ወይም በሌላ የባለቤትነት ማስተላለፊያ ዘዴ የማቅረብ፣

ሠ. ኦሪጅናል ክዋኔውን ወይም ቅጅውን ለኪራይ ወይም ለሕዝብ ውሰት የማቅረብ፣

ረ. ግዙፍነት ያገኘ ክዋኔን በሽቦ ወይም በሽቦ አልባ መንገድ የህብረተሰቡ አባላት በተናጠል በመረጡት ቦታ ወይም በመረጡት ሰዓት እንዲደርሳቸው የማድረግ፣



፪/ ከዋኙ ክዋኔው በቪዥዋል ወይምኦዶዮቪዥዋል መልክ እንዲካተት ከፈቀደ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) ተፈፃሚነት የለውም፣

፫/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም የአንድ ትዕይንት ወይም ሥራ ወይም ኦዶዮቪዥዋል ሰነድ ዋነኛ ጉዳይ የሆነ ክስተት ደጋፊ የሆነ ክዋኔን ማባዛትና ለሕዝብ ማቅረብን ከዋኙ መከልከል አይችልም፣

፬/ ከዋኙ ከኢኮኖሚያዊ መብቱ ውጪ ወይም ይህንኑ መብት ካስተላለፈም በኋላ የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፣

ሀ. የክዋኔው አጠቃቀም የከዋኙን ማንነት መጥቀስ የማያስችል ካልሆነ በቀር ክዋኔው በቀጥታ ሲተላለፍ ወይም በድምፅ ሪከርዲንግ ሲቀረፅ ማንነቱ እንዲታወቅ የማድረግ፣

ለ. በሥራው ላይ የሚደረግ ማንኛውንም መዛባት፣ መቆራረጥ ወይም ሌላ ማሻሻያ ስሙንና ክብሩን የሚጎዳ ከሆነ የመቃወም፣

ሐ. የዚህ አዋጅ አንቀፅ ፰ (፪) እና (፫) ድንጋጌዎች እንደአግባቡ በዚህ አንቀፅ በተመለከተው የከዋኝ መብት ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ::

፭/ በዚህ ክፍል የተመለከቱት መብቶች ክዋኔው በድምፅ ሪከርዲንግ ግዙፍነት ካገኘበት ወይም ግዙፍነት በሌለ ጊዜ ክዋኔው ከተፈፀመበት ዓመት መጨረሻ ጀምሮ ለ፶ ዓመት ፀንቶ ይቆያል::

### ፳፯. የድምፅ ሪኮርድ ፕሮዲውሰር ብቸኛ መብቶች

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፳፰ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የድምፅ ሪኮርድ ፕሮዲውሰር የሚከተሉትን ለመፈፀም ወይም ሶስተኛ ወገን እንዲፈፅማቸው ለመፍቀድ ብቸኛ መብት ይኖረዋል፣

ሀ. በማንኛውም አኳኋን ወይም መልክ የድምፅ ሪኮርዱን የማባዛት፣

ለ. የድምፅ ሪኮርዱን ቅጅዎች ወደ ሀገር ውስጥ የማስገባት፣

ሐ. በሽያጭና መሰል የባለቤትነት ማስተላለፊያ መንገድ በፕሮዲውሰሩ ፈቃድ ለስርጭት ያልቀረበ የድምፅ ሪኮርዲንግ ኦሪጅናል ወይም ቅጂውን ለሕዝብ የማሰራጨት፣

መ. ለኪራይ ወይም ለውሰት የቀረበ ቅጂ ላይ ያለ ባለቤትነት ከግምት ሳይገባ የድምፅ ሪኮርድ ቅጅ ለሕዝብ በኪራይ ወይም በውሰት የማቅረብ፣

ሠ. የድምፅ ሪከርዲንግን በሽቦ ወይም በሽቦ አልባ መንገድ የሕብረተሰቡ አባላት በተናጠል በመረጡት ቦታ ወይም ሰዓት እንዲደርሳቸው የማድረግ፣

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተደነገገው መብት የታተመ የድምፅ ሪከርዲንግ ሲሆን ከታተመበት ዓመት የመጨረሻ ቀን ወይም የድምፅ ሪከርዲንጉ ያልታተመ ሲሆን ግዙፍነት ካገኘበት ዓመት የመጨረሻ ቀን ጀምሮ ለ፶ ዓመት ፀንቶ ይቆያል::

፳፰. የድምፅ ፕሮዲውሰር ግዴታዎች

፩/ ማናቸውም የድምፅ ሪከርዲንግ ወይም የኦዲዮቪዡዋል ሥራ ፕሮዲውሰር በሪከርዲንግ ሌብሉ ወይም በመያዣው ላይ የሚከተሉትን መጥቀስ አለበት፣

ሀ. የሥራውን ወይም የሥራዎቹን ርዕስ፣
ለ. የሥራ አመንጪውንና የዋነኛ ከዋኞቹን ስም፣
ሐ. የፕሮዲውሰሩ ስም ወይም መለያ ምልክት፣ እንዲሁም፣
መ. በዚህ አዋጅ መሠረት ፕሮዲውሰሩ ያገኘው መብት የተጠበቀ ስለመሆኑ፣

፪/ ለዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) (ለ) ዓላማ አንድ የሙዚቃ ቡድን ወይም ኦርኬስትራ በስሙ እና መሪ በኖረ ጊዜ በመሪው ስም ይጠራል::

፳፱. ስለ መብት ጥበቃ ማስታወቂያ

፩/ የኦዲዮቪዡዋል ወይም የድምጽ ሪከርዲንግ ቅጂ ለንግድ ዓላማ እንዲውል ሲዘጋጅ ሌብል ወይም መያዣው ፕሮዲውሰሩ የመብት ጥበቃ ያለው መሆኑን በበቂ ሊያሳውቅ በሚችል አኳኋን የተቀመጠና፣

ሀ. የ (p) ን ምልክት እና
ለ. ሪከርዱ ለመጀመሪያ ጊዜ የታተመበትን ዓመት የያዘ ማስታወቂያ ይታተምበታል፣

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተመለከተው ማስታወቂያ የፕሮዲውሰሩን መብት በተመለከተ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚቀርቡ ክርክሮች ላይ ፍሬ ነገርን የሚያስረዳ መነሻ ማስረጃ ይሆናል::

፴. የድምፃ ሪከርዲንግ ለመጠቀም የሚፈፀም ክፍያ

፩/ ለንግድ ዓላማ የታተመ የድምፅ ሪከርዲንግ ወይም ቅጅው በቀጥታ በብሮድካስቲንግ ወይም ሌላ ለሕዝብ ከቀረበ ወይም በይፋ ከተከወነ ተጠቃሚው ለከዋኙ፣ ለድምፅ ሪከርድ ፕሮዲውሰሩ ተመጣጣኝ ክፍያ አንድ ጊዜ ይከፍላል፣



፪/ በከዋኙና በፕሮዲውሰሩ መካከል የተለየ ስምምነት ከሌለ በቀር የድምፅ ሪከርዲንግ ፕሮዲውሰሩ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) መሠረት ካገኘው ገቢ ላይ ግማሹን ለከዋኙ ይከፍላል፣

፫/ በዚህ አንቀፅ የተደነገገውን ተመጣጣኝ ክፍያ የማግኘት መብት የድምፅ ሪከርዲንጉ ከታተመበት ጊዜ ጀምሮ ወይም የድምፅ ሪከርዲንጉ ያልታተመ በሆነ ጊዜ ግዙፍነት ካገኘበት ቀን ጀምሮ ለ፶ ዓመት ፀንቶ ይቆያል::

፴፩. የብሮድካስቲንግ ድርጅትን ፈቃድ የሚጠይቁ ድርጊቶች

፩/ ማንኛውም የብሮድካስቲንግ ድርጅት የሚከተሉትን ለመፈፀም ወይም እንዲፈፀሙ ለመፍቀድ ብቸኛ መብት ይኖረዋል፣

ሀ. ብሮድካስቱን እንደገና ብሮድካስት የማድረግ፣
ለ. ብሮድካስቱ ግዙፍነት እንዲያገኝ የማድረግ፣
ሐ. ግዙፍነት ያገኘውን ብሮድካስቱን የማባዛት

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተደነገገው መብት ብሮድካስት ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ ለሃያ ዓመት ፀንቶ ይቆያል::

፴፪. የመብት ገደቦች

በዚህ አዋጅ ከአንቀፅ ፳፮ እስከ ፴፩ ያሉት መብቶች ከሚከተሉት ድርጊቶች ጋር በተያያዘ ተፈፃሚነት የላቸውም፣

ሀ. ወቅታዊ መረጃ ለማቅረብ አስፈላጊ እስከሆነ ድረስ ከአንድ ሥራ ላይ በአጭሩ የተወሰዱ መጣጥፎችን ለወቅታዊ ሁኔታ ዘገባ የመጠቀም፣
ለ. ለሳይንሳዊ ምርምር ዓላማ የማባዛት፣
ሐ. ለማስተማሪያነት ወይም ማብራሪያ ለመስጠት የታተሙ ክንዋኔዎች ወይም የድምፅ ሪከርዲንግን ሳይጨምር ፊት ለፊት ለማስተማር ዓላማ የማባዛት ብቻ፣
መ. በክፍል ሁለት በተጠቀሰው መሠረት አንድን ሥራ ያለ አመንጪው ወይም ሌላ የቅጅ መብት ባለቤቱ ፈቃድ መጠቀም በሚቻልባቸው ሁኔታዎች፣

ክፍል ስድስት
ስለመብቶች ተፈፃሚነት

፴፫. በጊዜያዊነት ስለሚወሰዱ እርምጃዎች

፩/ ፍርድ ቤት፣

ሀ. በቅጂ ምክንያት የሚፈጠርን የመብት ገሰሳ ለመከላከል በተለይም የግምሩክ ክሊራንስን ጨርሰው ወደ አገር ውስጥ የሚገቡትን ጨምሮ እቃዎች ወደ ንግድ ውስጥ እንዳይገቡ ለማድረግ፣

ለ. ተፈፀመ የተባለን የመብት ገሰሳ የሚያስረዳ አግባብነት ያለውን ማስረጃ ለመጠበቅ ፈጣንና ውጤታማ የጊዜያዊ እርምጃ ትእዛዝ መስጠት አለበት፡፡

፪/ ፍርድ ቤቱ አግባብ ሆኖ ሲገኝ በተለይም መዘግየቱ በባለመብቱ ላይ ሊተካ የማይችል ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ከሆነ ወይም ማስረጃ እንደሚጠፋ በግልፅ የሚታይ አደጋ ካለ ሌላው ወገን ሳይሰማ ጊዜያዊ እርምጃ የመውሰድ ሥልጣን አለው፣

፫/ ተከሳሹ መብት ከመጣስ እንዲታቀብ በቀረበ ክስ ላይ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ ከሳሹ የመብት ገሰሳን ለማስቆም ጊዜያዊ የእግድ ትእዛዝ እንዲሰጥ ፍርድ ቤቱን መጠየቅ ይችላል፡፡ ፍርድ ቤቱም፣

ሀ. በእግድ ትእዛዝ ጥያቄው ላይ ለመወሰን አደጋ ላይ የወደቀው ጥቅም በካሳ ሊሸፈን የማይችል መሆኑን፣ አደጋው የማይቀር መሆኑን፣ የክሱን ጥንካሬና ውሳኔ መስጠት በእያንዳንዱ ተከራካሪ ወገን ላይ የሚያስከትለውን ጉዳት መመርመር አለበት፣

ለ. የእግድ ትእዛዙን ሊሰጥና አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው እግዱ የሚቆይበትን ጊዜ፣ ተከሳሹ የሚያስፈልገውን ገንዘብና ዋስትና ወይም ሌሎች ጉዳዮች ሊያመለክት ይችላል፣

ሐ. ከፍ ሲል በተመለከተው መመዘኛ ተከራካሪዎች ሲመዘኑ በእኩል ደረጃ በሆኑ ጊዜ ጊዜያዊ እግድ ከመስጠቱ በፊት አንፃራዊ ጥንካሬያቸው ላይ ጥልቅ ምርመራ ማድረግ ይችላል፣

፬/ በዚህ አዋጅ ጥበቃ ያገኘን መብት የሚጥስ ተግባር በተፈፀመ ጊዜ ብርበራና ዕቃ መያዝን የሚመለከቱ የፍትሐብሄር ሥነ ሥርዓት ሕግና የወንጀል ሥነ ሥርአት ሕግ ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል

፭/ ፍርድ ቤቱ አመልካች የመብት ባለቤት መሆኑን እና መብቱ መጣሱን ወይም ሊቀር የማይችል የመብት መጣስ አደጋ መኖሩን፣ በበቂ ደረጃ ሊያሳምን የሚችል ማስረጃ እንዲያቀርብ እና ተከሳሹን ከጉዳት ለመጠበቅ አመልካቹ መያዣ ወይም ተመጣጣኝ ዋስትና እንዲያቀርብ የማዘዝ ሥልጣን ይኖረዋል፣

፮/ ሌላው ወገን ሳይሰማ ጊዜያዊ እርማጃ በተወሰደ ጊዜ በእርምጃው የተጎዳ ወገን እርምጃው ተፈፃሚ እንደሆነ ወዲያውኑ እንዲያውቀው መደረግ አለበት፡፡ እርምጃው ከተገለፀ በኋላ ተከሳሹ ጥያቄ ባቀረበ ጊዜ የተወሰደውን እርምጃ ለማሻሻል፣ ለመሻር ወይም ለመለወጥ የሚያስችል ውሳኔ ለመስጠት የመስማት መብት ጨምሮ በቂ ጊዜ በመስጠት ጉዳዩ እንደገና መታየት አለበት፣



፯/ ጊዜያዊ እርምጃው የተሻረ ወይም አመልካቹ በፈፀመው ወይም ሳይፈፅመው በቀረ ድርጊት ምክንያት እርምጅው ሳይፈፀም የቀረ ከሆነ ወይም ውሳኔው ከተሰጠ በኋላ የተጣሰ ወይም የመጣስ አደጋ ያጋጠመው መብት የሌለ መሆኑ ከታወቀ በተከሳሹ ጠያቂነት ለደረሰበት ጉዳት በቂ ካሳ እንዲከፈለው ፍርድ ቤቱ ማዘዝ አለበት፡፡

## ፴፬. <u>የፍትሐብሄር መፍትሄዎች</u>

፩/ በዚህ አዋጅ የሚነሱ የፍትሐብሄር ጉዳዮችን አስመልክቶ የዳኝነት ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት የመብቱ ባለቤት ያወጣውን ወጪ ጨምሮ ለደረሰበት ቁሳዊ ወይም ሞራላዊ ጉዳት በቂ ካሳ እንዲከፈለው የማዘዝ፣ ጊዜያዊ እግድ መስጠት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ከዚህ በታች የተመለከተውን ጨምሮ ማንኛውንም ተገቢ ነው ብሎ ያመነበትን ትእዛዝ መስጠት አለበት፣

ሀ. በዚህ አዋጅ ጥበቃ ያገኘ መብት እንዳይጣስ የመከላከል ወይም የመብት መጣስ እንዲቆም ጊዜያዊ እግድ የመስጠት፣

ለ. ቅጅን የመስራት ወይም ወደ አገር ውስጥ የማስገባት ድርጊት የባለቤቱ ፈቃድ የሚያስፈልገው ሲሆን ያለ ባለቤቱ ፈቃድ የተሰራ ወይም ወደ ሀገር ውስጥ የገባ ሥራን እንዲወርስ የማዘዝ፣

ሐ. ከቅጂዎች ጋር የተያያዙ ሰነዶች፣ የሂሳብ መግለጫዎች ወይም የንግድ ሥራ ለማከናወን የሚያስፈልጉ ወረቀቶችን ለመስራት የሚያገለግሉ መሳሪያዎችና እሽጎች እንዲያዙ ትእዛዝ የመስጠት፣

፪/ የቅጅ መብት ወይም የተዛማጅ መብት ባለቤት በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) ከተመለከተው ካሳ በምትክ ወይም በአማራጭ ከመብት መጣሱ አላግባብ የተገኘ ብልፅግና እንዲተካለት ሊጠይቅ ይችላል፣ መብት ጣሹ በባለቤቱ ፈቃድ ቢሰጠው ኖሮ ፈቃዱን በመጠቀሙ ምክንያት ይከፍለው የነበረውን የህል አላግባብ እንደበለፀገ ይቆጠራል፣

፫/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፪) ቢኖርም የመብቱ ባለቤት በመብት ጣሹ የተገኘ የተጣራ ትርፍ ብቻ እንዲከፈለው ሊጠይቅ ይችላል፡፡ በዚህ ጊዜ መብት ጣሹ ያገኘውን የተጣራ ትርፍ ለመወሰን ሂሳብ የሚሰራ ሲሆን ትርፉ በሌሎች የገበያ ሁኔታዎች ምክንያት የተገኘ መሆኑን የማስረዳት ሀላፊነት የመብት ጣሹ ይሆናል፣

፬/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ለደረሰ ቀሳዊ ጉዳት የሚከፈል ካሳ መጠን የመብት ባለቤቱ የደረሰበትን የገንዘብ ጉዳት እና በመብቱ መጣስ ምክንያት የተገኘ ትርፍን ግምት ውስጥ በማስገባት ይወሰናል:: ለሞራል ጉዳት የሚከፈል ካሳ ከብር ፩፻ሺ (አንድ መቶ ሺ ብር) የማያንስ ሆኖ የደረሰውን ጉዳት መሠረት በማድረግ ይወሰናል፣

፭/ የመብት መጣስ ድርጊት የፈፀመው ሰው ድርጊቱን ያላወቀ ከሆነ ወይም ሊያውቅ የሚያስችለው በቂ ምክንያት የሌው ከሆነ ፍርድ ቤቱ ካሳው ከድርጊቱ በተገኘ ትርፍ ላይ ብቻ እንዲወሰን ሊያደርግ ይችላል፣

፮/ መብት የጣሱ ቅጂዎችና ቁቅሎች መኖራቸው የታወቀ ከሆነ ባለቤቱ በተቃራኒው ካልጠየቀ በቀር ፍርድ ቤቱ ቅጂዎቹ በባለቤቱ መብት ላይ ጉዳት ሳያደርሱ ከንግድ እንቅስቃሴው ውጭ እንዲሆኑ ወይም እንዲወገዱ ወይም በሌላ ተገቢ አኳኋን እንዲጣሉ ለማዘዝ ይችላል:: ይህ ድንጋጌ ቅጂዎቹንና ጥቅሉን በቅን ልቦና በያዘ ሶስተኛ ወገን ላይ ተፈፃሚ አይሆንም::

## ፳፩. የድንበር ላይ እርምጃዎች

፩/ የጉምሩክ ባለሥልጣን የቅጅ መብት ወይም ተዛማጅ መብት ባለቤት በሚያቀርበው ማመልከቻ መሠረት አመልካቹ መብቱን የጣሱ ናቸው ብሎ ያመነባቸው ዕቃዎችን በቁጥጥሩ ሥር መያዝ ይኖርበታል፣

፪/ የጉምሩክ ባለሥልጣኑ ዕቃውን ለመያዝ የወሰደውን እርምጃ በተመለከተ ለአመልካቹ ወይም ለዕቃው ባለቤት ወዲያውኑ ያሳውቃል፣

፫/ አመልካቹ ዕቃው ስለመያዙ ከተገለፀበት ቀን ጀምሮ ባሉት አስር ቀናት ውስጥ ተገቢውን ህጋዊ ማስረጃ ማቅረብ ካልቻለ ዕቃውን ለመያዝ የተወሰደው እርማጃ ይነሳል፣

፬/ ዕቃ እንዲያዝ የቀረበው ማመልከቻ ህጋዊ መሠረት የሌለው መሆኑ ሲረጋገጥ ዕቃው በመያዙ ምክንያት ለሚደርሰው ጉዳት አመልካቹ ተጠያቂ ይሆናል፣

፭/ በፍርድ ቤት ትእዛዝ መሠረት የጉምሩክ ባለሥልጣን መብት የጣሰን ዕቃ መውረስ ይችላል፣



## ፳፪. የወንጀል ቅጣት

፩/ በወንጀል ሕግ የበለጠ ቅጣት የሚያስቀጣ ካልሆነ በቀር በዚህ አዋጅ ጥበቃ ያገኙ መብቶችን ሆነ ብሎ የጣሰ ማንኛውም ሰው ከ፭ ዓመት በማያንስ እና ከ፲ ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሥራት ይቀጣል፣

፪/ በወንጀል ሕግ የበለጠ ቅጣት የሚያስቀጣ ካልሆነ በቀር በዚህ አዋጅ ጥበቃ ያገኙ መብቶችን ከፍ ባለ ቸልተኝነት የጣሰ ማንኛውም ሰው ከ፩ ዓመት በማያንስ እና ከ፭ ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሥራት ይቀጣል፣

፫/ አግባብነት ባለው ጊዜ ቅጣቱ ወንጀሉን ለመፈፀም ያገለገሉ እቃዎች ወይም መሳሪያዎች እና መብት የጣሱ ዕቃዎችን መያዝ፣ መውረስ እና ማውደምን ይጨምራል::

## ክፍል ሰባት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## ፳፫. ተፈጻሚነት ባላቸው ሕጎች ጥበቃ ስላላቸው ሥራዎች

፩/ ይህ አዋጅ ተፈፃሚ ከመሆኑ በፊት በነበሩና የጥበቃ ጊዜያቸው ፀንተው በሚገኙ ሥራዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ፣

፪/ ይህ አዋጅ ተፈፃሚ ከመሆኑ በፊት በተደረጉ ሥራን የሚመለከቱ ውሎች ላይ ተፈፃሚነት የለውም::

## ፳፬. ተፈፃሚነት የሌላቸው ሕጎች

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውንም ሕግ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት የለውም::

## ፳፭. ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈፀም ደንብ ሊያወጣ ይችላል፣

፪/ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጣውን ደንብ ለማስፈፀም ፅህፈት ቤቱ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል::

**አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሰኔ ፲፯ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት